የደገፍኩት ትግሉን እንጂ
ግለሰቡን ኃይሉ አልነበረም

በዋሽንግተን ዲሲ የኢትዮጵያዊነት ድርጅት አካል የሆነው የኢትዮጵያዊነት ሬዲዮ አዘጋጅና በአንድ ወቅት የኢንጂነር ኃይሉና የድርጅታቸው ሁነኛ ደጋፊና ምርኩዝ በመሆን ብዙ ተቃዋሚና ወዳጆችን ያፈራው አቶ ምርጫው ስንሻው አሁንም መስመር ላይ ነው። በወቅቱ የአቶ ኃይሉ ሻውል አነጋጋሪ የስምምነት ውሳኔ ላይ ምን ይላል? ዘኢትዮጵያ ጋዜጣ አነጋግሮታል።

ዘኢትዮጵያ- የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል በተለይ አቶ ኃይሉ ሻውልን የጨመረ አንድ ድርድርና ስምምነት መደረጉ እየተወራ ነው በዚህ ላይ ያንተ አቋም ምንድነው?

አቶ ምርጫው- እንደማገኘውም ኢትዮጵያዊ ጉዳዩን ተከታትየዋለሁ። የወጡትንም ሰነዶች አንብቤያለሁ። በሰነዱ ላይ የተባሉት ነገሮች በሙሉ በህገመንግሥቱ ውስጥ የተካተቱ ናቸው። ቀደም ብሎም አስፈጻሚ ቢኖረው ኖሮ በህገመንግሥቱ ውስጥ ያሉ የማንም ሰው የሆኑ መብቶች ናቸው። ምንም አዲስ ነገር የለም። ከ1992 ጀምሮ ምርጫ ሁለተኛ ሶስተኛ ምርጫ ተካሂዷል። ምንም እንከን የሌለበት ምርጫ እናካሂዳለን ተብሎ ቃል ከተገባለት በኋላ ምን ያክል ሰው እንደተፈናቀለ፣ እንደተሰደደ፣ እንደሞተ፣ በጥይት እንድተደበደበ፣ የምናውቀው ስለሆነ እኔ ዛሬ እነኚህ ሰዎች ይህንን መፈራረማቸው በእውነት የተለየ በጆሯቸው የነገሯቸው ነገር ከሌለ በስተቀር ለኔ ወያኔ ከዚህ የተለየ የሚሰጠው ነገር ተገኝቶ ነው ብዬ አላምናም። እና እስካሁን ድረስ ግራ እንደገባኝ ነው።

ዘኢትዮጵያ- - መጨባበጣቸው በራሱ እንደታሪካዊ ነገር እየተወራ ነው።

አቶ ምርጫው- የመጨባበጡንም ጉዳይ ቀላል ነገር አናድርገው። መለስ፣ ኃይሉ ሻውልን ዝም ብሎ ይጨብጣል ብዬ በምንም መንገድ ላምን አልችልም። "ከመለስ ዜናዊ ጋር አልደራደርም፣ መለስ ዜናዊ አምባገነን መንግሥት ነው፣ መለስ ዜናዊ ብቻውን ነው ያለው፣ እንደመንግሥት እሱን ሪኮግናይዝ አድርገን እንደራደረውም" ሲባል የነበረው በእነ አቶ ኃይሉ ሻውል ነው። እነሱ ሄደው ለመጨባበጥ ካደረሳቸው፣ ከመጨባበጡ ጀርባ ምንድነው ያለው? በርግጥ በ1997 የተደረገውን ምርጫ ዓይነት ችግር አይፈጠርም ብሎ ዓለም አቀፉን ህብረተሰብ ለማታለል ትልቅ መሳሪያ ሆኖ አገልግሎታል። እንጂ መለስ በ18 ዓመት ባየነው ባህሪው፣ ስለ ብሔራዊ እርቅ፣ ስለሰላም፣ ስለፍቅር ተብሎ በተሰበኩ ነገሮች ላይ፣ አይተነዋል። በእንዲህ ዓይነት ስምምነት የሚያምን ሰው አይደለም።

ዘኢትዮጵያ-- ከአቶ ኃይሉ ሻውል ድርጅት ጋር አሁን ያለህ ግንኙነት ምንድነው?

አቶ ምርጫው- ድርጅቱ መኢአድ ኢንጂነር ኃይሉ፣ ከዚህ ወደ ዋሽንግተን መጥተው ከሄዱ በኋላ ችግር እንደገጠመው አውቃለሁ። በጣም በቅርበት ተጠግቼ ምን ይካሄድ እንደነበር አውቃለሁ፣ እሳቸው መጥተው ከሄዱ በኋላ ስምምነት የለም። እንደተከፋፈለ ነው። ቻፕተሮች ተለያይተዋል። በጣም በጣም ጠንካራ የሆኑና መሥራት የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን የመኢአድ ሰዎች አቶ ኃይሉን ጨምሮ የድርጅቱ አባላት ላይ፣ ባደረጉት ተጽእኖ ምክንያት፣ተከፋፍለዋል። ዛሬ ሰሜን አሜሪካ ያለውን ሁኔታ ነው ልነግርህ የምችለው። ውስጡ ችግር አለ። ያ ችግር ይህን ውይይት አሁን እስከምናደርግበት ድረስ አለመፈታቱን አውቃለሁ። ወደፊትም ምናልባት አሁን ይህ ሁኔታ፣ አብዛኛውን እንዲነቃ ፣ እንዲሰባሰብ አድርጎት፣ ምን ማድረግ አለብን ብሎ ተወያይቶ

የሚስተካከለውን አስተካክሎ ችግሩን ፊቶ ካልተንቀሳቀሰ አሁን ይሄ ነው የሚል የሚያስመካ ነገር አላይም።

ዘኢትዮጵያ- የአቶ ኃይሉን መኢአድን ወክሎ  የሚንቀሳቀስ ድርጅት እዚህ የለም እያልከኝ ነው?

አቶ ምርጫው- ትክለለኛ የፖለቲካ ውክልና  ተሰጥቶት የሚንቀሳቀስ ማን እንደሆነ አላውቅም። እኔነኝ እኔ ነኝ የሚሉ ግን ግን አራት ያክል ቡድኖች አሉ።
ዘኢትዮጵያ-- እዚህ አካባቢ እነ አቶ አባይነህና እነ ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት አሉ። ዶ/ር ታዬ በትግሉ ውስጥ ብዙ መስዋእትነት የከፈሉ፣ ስምም ያላቸው ሰው ናቸው። የድርጅቱ የአማካሪ ቦርድ ሆነው እንደሚሰሩና የአቶ ኃይሉ ደጋፊና የድርጅቱ ሁነኛ ሰው እንደሆኑ ነው የማውቀው። መግለጫዎችንም እየሰጡ ነው። እና አቶ ኃይሉ ብቻቸውን ናቸው ምንም እንቅስቃሴ እዚህ አካባቢ የለም ብሎ መናገር ይቻላል? እነ ዶ/ር ታዬን የሚያህል ሰው ካለበት ማለቴ ነው?

አቶ ምርጫው- በመጀመሪያ አቶ አባይነህ እዚህ መጥተው የቀሩ ናቸው። ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሱ አይደሉም። የሳቸውን እንተወው። ነገ የምናየው ነው። አንተ እንደምትለው ሁሉ እኔም ለእነ ዶ/ር ታዬ ከፍ ያለ አክብሮት ነበረኝ። መቸም የሚከበረው ትግሉ ነው። ትግሉን ደግሞ የሚያስተባብርልህን ሰው አብረህ ታከብራለህ። ዶ/ር ታዬ ወደዚህ ታስሮ ሲመጣ እጁን አጨብጭቦ የተቀበለውና በትግሉ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል በማለት፣ እሱንም ወደ ቅንጅቱ ለማምጣት ብርቱ ጥረት ተደርጓል። እንዲያውም ከቅንጅቱ ምስረታ በፊት፣ በከፍተኛ ደረጃ በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወረ፣ ቅንጅትን ይወቅሳል፣ ይሰድባል፣ ይባል በነበረበት ጊዜ፣ እነ ሻለቃ አድማሴና እነ ዶ/ር በዛብህ ወደዚህ በመጡበትና በቅንጅት መካከል የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ጥረት በሚደረግበት ጊዜ፣ የተቋቋመውን ኬ.አይ.ሲ. የተባለውን ዓለም አቀፍ የቅንጅት ካውንስል የሚባለውን ለማቋቋም ጥረት ባደረጉበት ጊዜ፣ ሁሉም ዶ/ር ታዬን በዚህ ውስጥ እንዲያካትቱት ለማድረግ፣ ሁላችንም በየበኩላችን ግፊት አድርገናል። በመጨረሻም እሱም ቢሆን ፈቃደኝነቱ ተጠይቶ፣ ፈቃደኛ ሆኖ፣ ኬ.አይ.ሲ.ን ለመምራት ኃላፊነቱን ተረክቦ ነበር። ዛሬ ግን የመኢአድ ቻፕተሮችን እንኳ እንዳይመራ የታገደ ሰው ነው። ይልቁንስ ዶ/ር ታዬን ካነሳኸው ዘንዳ፣ በእውነት ስለ እውነት ኢትዮጵያዊው ማወቅ ካላበት፣ ቅንጅትን ያለምንም መስዋዕትነት፣ ያለፋበትን ድርጅት፣ በወርቅ ሰሀን የተቀበለ ሰው፣  ያውም በኃላፊነት ለመምራት የተቀበለ ሰው፣ ዶ/ር ታዬ ነው።

ዘኢትዮጵያ-- ምንድነው "የተቀበለ" ማለት፣ ምንድነው የሚቀበሉት ምንስ ነው የተቀበሉት?

አቶ ምርጫው - እሱን ልገልጽልህ ነው። ዶ/ር ታዬ ቅንጅትን ሲቀበል ዝምብሎ አይደለም የተቀበለው፣ እዚህ አካባቢ በተለይ በሰሜን አሜሪካና አውሮፓ የሚገኙ፣ 22 የሚሆኑ የኢትዮጵያን ፖለቲካ የተረዱ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት በመታገላቸው የሚታወቁ 22 ሰዎች ተጨምረው ጽ/ቤት፣ ስልክ፣ ኮምፒውተር፣ የእጅ ስልክ ሁሉ እስከ ትራንስፖርት ድረስ ታስቦለት፣ በተቻለ መጠን ትግሉን እንዲመራና እንዲያስተባብር ተብሎ፣ እድል ከተሰጣቸው በጣም ጥቂት ኢትዮጵያውያን አንዱ ነው። ከሱ ሌላ ጠንካራ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ትግል እንዲመሩ እድል የተሰጣቸው ሶስት አራት ሰዎች አይሆኑም እዚህ ከተማ። ምናልባትም እነ ኮ/ነሹ ወልዴ ባንድ ወቅት። ከዚያ በስተቀር ግን ብዙዎቹ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ዶ/ር ታዬ ያገኘውን እድል አላገኙም። ይህ ሁሉ ተሟልቶለት፣ 22ቱ ሰዎች ብዙዎቹን አውቃቸዋለሁ። አነጋግሬያቸዋለሁም። ከሁለት ጊዜ በላይ ስብሰባ አላደረጉም። ኬ.አይ.ሲ. የሚባለው ነገር ሲበተን ሁላችን ሲቋቋም ተቋቋም ብለን የተናገረውን ያክል ሲፈርስ ግን ለምን እንደፈረሰ እንዴት እንደፈረሰ እንኳ መግለጫ ሳይሰጥ፣ እጁ ላይ ነው የፈረሰው፣ እስከዛሬ ድረስ ኢትዮጵያዊው ኬ.አይ.ሲ. የሚባለው፣ የቅንጅት ዓለም

አቀፍ ማእከል የሚባለው ነገር ካውንስሉ እንዴት እንደፈረሰ ለምን እንደፈረሰ ይፋ የሆነ መግለጫ እስካሁን ድረስ አልተሰጠበትም።

ከዚያም ተመሳሳይ ነገር አለ። ለምሳሌ በዚሁ በቅንጅት ግብግብ ጊዜ በየቦታው ተነስተው የነበሩት ቻፕተሮች፣ ደህና ይንቀሳቀሱ የነበሩት ቻፕተሮች ፈራርሰው ነበር። ኢንጂነር ኃይሉ ወደዚህ ወደ ሰሜን አሜሪካ በመጡበት ጊዜ፣ እነዚህን ቻፕተሮች ለማቋቋም 12 አባላት ያሉት ግብረኃይል ተቋቁሞ ነበር። ያ ግብረኃይል የሚመራው በዶ/ር ታዬ ነበር። ግብረኃይሉ ከተቋቋመ በኋላ፣ ሁለት ቀን ተሰብስቦ፣ አንደኛው በኢንጂነር ኃይሉ አስገዳጅነት ተሰብስቦ፣ ሁለተኛው በሌላ ጉዳይ ተሰብስቦ ከዚያ በኋላ አልተሰበሰበም። የሚያሳዝነው ግብረኃይሉ እንኳ ተሰብስቦ ለኢንጂነር ኃይሉ ሪፖርተር አላደረገም። ኢንጂነር ኃይሉን ራሳቸውን ጠይቄያለሁ። ለምንድነው ይሄ ነገር ግብረኃይል ከተቋቋመ ለሕዝቡ ግብረኃይሉ መቋቋሙ ከታወቀ በኋላ፣ ግብረኃይሉ መኖሩ አለመኖሩ ፈረሰ ሠራ አልሠራ የሚለው ነገር ለምንድነው የማይገለጸው ብዬ ስላቸው፣ ራሴ ተዘዋውሬ እንዳየሁት፣ ይሄ ነው ተብሎ የተገለጸለኝ ቻፕተሮች ተብሎ የተገለጸልኝ ነገር፣ የት ቦታ ምን ቦታ እንዳለ በ ዓይኔ ያየሁት ነገር ስለሆነ፣ ከዚህ ግብረኃይል ምን እጠብቃለሁ በማለት ዶ/ር ታዬ ይመራ የነበረው ግብረኃይል፣ ሁላችንም በአባልነት የተሳተፍንበት ግብረኃይል ሜዳ ላይ ተበትኖ ቀርቷል። ያ ብቻ አይደለም ዶ/ር ታዬ ይህን አመራር ከተረከበ ጊዜ ጀምሮ፣ አብዛኛው ኢትዮጵያ የሚውያቀው የትንሳዔ ሬዲዮ ነበር። የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ የሚባል ኢትዮጵያ የሚደመጡ ሁለት ሬዲዮኖች ነበሩ። ሁለቱን ሬዲዮኖች አንድ ላይ እናዋቅራለን ጥረት እያደረግን ነው ተብሎ መሃል ላይ እንዴት ለምን ሳያባል በመካከል ሁለቱም እንዲዘጉ ተደረገ። የቅንጅት ዋናው ዌብ ሳይት ይባል የነበረው ቅንጅት ዳት ኦርግ ከኤዲቶሪያል ቦርዱ ጋር እሱ ሳይስማማ በመቅረቱ ምክንያት ተበትኗል። ያኛውም እንዳልሆነ ሆኖ ቀርቷል። ሌላ ያ ብቻ አይደለም እዚህ ከተማ ያሉ ሬዲዮኖች የህብረት ሬዲዮ፣ የነጻነት ለኢትዮጵያ ሬዲዮን ውሰድ፣ የእኛ ኢትዮጵያዊነት ሬዲዮን ውሰድ፣ ሌሎች ዌብሳይቶች አሉ ለምሳሌ፣ እንደ ኢትዮ ላይን፣ ናዝሬተ ዳት ካም፣ እንደ ደብተራው ያሉ ዌብሳይቶች በሙሉ ዶ/ር ታዬን ለመርዳት ብዙ ጥረት አድርገዋል። ግን እንደምንፈልገው ብቻ ሳይሆን፣ ባልተጠበቀ ሁኔታ፣ ለምን እንደሆን ሳይታወቅ፣ የቅንጅት ነገር እንዳልሆነ ሆነ። ሌሎችም ፓልቶኮች፣ አሲምባ ፓልቶክ አለ፣ የዳይስፖራ ፓልቶክ አለ ሁሉም እሱን ለመርዳት ዝግጁዎች ነበሩ። ግን ይህ ሁሉ ነገር ተሟልቶለት፣ ምንም ሥራ ያልሠራና ምንም እንቅስቃሴ ያላደረገ ነው። ቢታወቅ በዓይን የሚታይ ይሄ ይሄ ተደረገ ተብሎ፣ የሚባል የለም ዛሬ በጁ ላይ ያለው ሶስት አራት ቦታ ቻርተሮች ተከፍለው፣ ዋናው የሚነጫነጩት ግሞሾቹ በዶ/ር ታዬ ምክንያት ነው። ይህንን ብዙ ሰው አይናገርም። ስለማይናገር ዝም ብለን እፍንፍን ብለን መሞት ነው። ያው በዚያ መንገድ እንቅስቃሴው እየተዳከመ ነው። ከዚህ በላይ ቅድም አንተ እንዳልከው ታስሮ ሲፈታ ከዚያ በፊት የመምህራን ማህበርን ይመራ በነበረበት ጊዜ፣ የአንጋፋው ድርጅት መሪ ተብሎ ነው የምናውቀው። ሁላችንም፣ በዚያ አክብሮት ይሠራል ያስተባብራል ብዙ ያደርግልናል ብለን ነው የጠበቅነው። ግን ማንም የፖለቲካ ድርጅት፣ ማንም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ እሱ የተሰጠውን እድል እሱ የተሰጠውን የሰው ኃይል የቁሳቁስና ማንኛውንም ነገር ተሟልቶ የማግኘት ጉዳይ እንደሱ ተሟልቶለት መንገድ ላይ የቀረ ነገር አላውቅም። ይልቁንስ በጆሮዬ የምሰማው ለማመን የሚጨንቀኝ፣ በሌሎች ሰዎች ሲገርመኝ የነበረው፣ አሁን ደግሞ በዶ/ር ታዬ የማየው፣ አንድ ቁምነገር ግን አለ።

ዘኢትዮጵያ-- ምድነው እሱ?

አቶ ምርጫው- በርግጥ ቁምነገር አይደለም። ግን የገረመኝ ነገር ነው። ለምሳሌ ተፈቶ እንደመጣ ሁሉም ሰው እንደሰማው “ይቺ ወያኔ፣ ያቺ ወያኔ” በማለት በአነስታይ ጾታ ስም “አንቺ” እያለ ነበር የሚጠራው። ሰሞኑን በሚሰጠው ተከታታይ መግለጫ ስሰማ ግን፣ ወያኔን “የኢትዮጵያ

መንግሥት፣ መንግሥት እንዳለው፣ ከመንግሥት ጋር በሚደረገው ድርድር" እያለ ሲናገር እየሰማሁ ነው። እንግዲህ ልብ አድርግ ይህ ሁሉ ነገር ለምን መጣ፣ ቀደም ብሎ ታስቦበት የሆነ ነገር ይሆን እንዴ ብዬ ሌሎች ሌሎች ነገሮችን እያነሳሁ እንዳነሳና እንደጠይቅ እያደረገኝ ነው። ለማንኛውም በሥራ በኩል ግን አንተ ያላየኸውን አንተ የማትነገረኝን ይሄ ይሄ ተሠርቷል ብዬ ለህብረተሰቡ ለመናገርና ለመዋሸት አልፈልግም።

ዘኢትዮጵያ-- ቀደም ሲል በተለይ በእስር በተፈቱ ጊዜ፣ በተለይም በአቶ ኃይሉ ሻውልና በሌሎቹ የቀንጅት አመራሮች መካከል ክፍፍል ይታይ በነበረ ጊዜ፣ የአቶ ኃይሉ ሻውልን ወገን ደግፈህ ትንቀሳቀስ እንደነበር ግልጽ ነው። አሁን ስታየው ያን ጊዜ ትሰጠው የነበረው ድጋፍ፣ ትክክል ነበረ ብለህ ታስባለህ?

አቶ ምርጫው- ከዚህ በፊት በተፈጠረው ክፍፍል፣ እንደሚታወቀው ኢንጂነር ኃይሉን፣ ከሚደግፉና ኢንጂነር ኃይሉ የሚሰጠውን አመራር ከሚከተሉ ወገኖች አንደኛው ነበርኩ። ያንን ሳደርግ ደግሞ ፣ ያኔም ያመንኩበት ዛሬም የማምነበትን ጉዳይ ነው ያደረግኩት። ክፍፍሉ የተፈጠረው፣ ያኔ ኬ አይ ኤል(KIL) የቀንጅት ዓለም አቀፍ አመራር፣ በሚባለው ውስጥ ባሉት ሰዎች አማካኝነት፣ ውስጥ ውስጡን ይሠራ በነበረው ደባና ተንኮል እንጂ ቅንጅት መትረፍ ይችል እንደነበር አውቃለሁ። ቅንጅት እንዲተርፍ ያን ጊዜ፣ መሪውን ማትረፍ አስፈላጊ ነበር። ኢንጂነር ኃይሉ በተለይ በሰሜን አሜሪካ ብቻ ሳይሆን፣ በኢትዮጵያ  ምን ያክል አክብሮት ያላቸውና፣ ትግሉንም ደግሞ ይመራሉ ያስተባበራሉ የሚል እምነት ሁላችንም እንደነበረን የታወቀ ነው። እንደሚታወቀው ከእስር ቤት ሲወጡ ፈርመው የወጡት ወረቀት ብዙ ሰው አሳዝኗል። የሆኖ ሆኖ ወጥተው ሥራ ይሠራሉ የሚል፣ ተስፋ ስለነበረ፣ በእነሱም ምክንያት ትግሉም አብሮ ታስሮ ስለነበረ፣ ቀጣይ የሆነ ነገር አይታይም ነበርና ጭንቀት ነበረን። እሳቸው ከእስር እንደወጡ፣ በተለይ ክፍፍሉም ሲመጣ፣ የእሳቸውን ፎቶ ግራፍ ለጥፈው፣ በስማቸው ስብሰባ እየተጠራ፣ እሳቸው ግን በስብሰባው እንዳይገኙ መደረጉ ትክክል አልነበረም። ሁለተኛ ደግሞ እሳቸው ወደ ዋሽንግተን በመጡበት ጊዜ፣ ለእነወይዘሪት ብርቱካን ሁለት ጊዜ ሽማግሌ ተልኮ፣ ለህክምና ወደዚህ መጥተዋል፣ ስብሰባ ተጠርቷል። ኑና ከህዝቡ ጋር ሆነን እንቀበላቸው ተብሎ ሁለቴ ሽማግሌ ሲላክ፣ አንቀበልም የዴሊጌሽኑ አባል አይደሉም፣ በማለት የድርጅቱን ሊቀመንበር አግልለዋቸው ስለነበር፣ ያ ተንኮልና ደባ ነው። እሳቸውን በዚያ ሁኔታ ከህዝቡ መነጠል ትክክል አይደለም ብለን፣ ቀጥ ብለን ረድተናቸዋል። ቅንጅት ውስጥ በመግባት ቅንጅት እንዲከፋፈል በሚደረገው ሥራ፣ እኛ ያቅማችንን ለማራገብ ሳይሆን፣ ያኔ ኢንጂነር ኃይሉን በመያዝ፣ በውስጣቸው ያለውን ችግር ራሳቸው ቁጭ ብለው ፈትተው፣ ሌሎች በግራና በቀኝ የሚጎትቷቸው ኃይሎች ተሰባሰበው እነሱ ቅንጅትን አትርፈውልን ያንን የተጋጋለ የህዝብ የትግል መንፈስ ይዘውልን ይሄዳሉ ነው። ለዚህ ደግሞ መሪውን ማትረፍ አለብን ነው። እና ያን ጊዜ ያደርግነው ትክክል ነው። አሁንም ቢሆን በመርህ ደረጃ፣ ዛሬም ነገም ትላንት እነመለስ፣ ኢትዮጵያን ለመበታተን በጎሳ ለማጠር፣ በክልል ለመሸንሸን እንዳደረጉት ሁሉ ዛሬ ኃይሉ ሻውል ያንን ያደርጋል አልልም። የሚከተሉት ወይም የተከተሉት የትግል ስልት ወይም የሚጠቀሙበት የትግል ታክቲካቸው፣ አሁን ያለበት ሁኔታ እስካሁን ድረስ ስላልገባኝ  በጣም አስቸጋሪ ነው። ግን የማውቀው አንድ ሀቅ አለ። ያ የማውቀው ሀቅ ወያኔ ምንም ቢሆን አዋርዶ የተወሰነ ጊዜ ተጠቅሞብህ፣ አንተተን አውርዶህ ከህዝብ ከሚከሰክስህ በስተቀር፣ አንተ በወያኔ ውስጥ ታቅፈህ የኢትዮጵያን ህዝብ ትግል አቀጣጥለህ ለድል ታበቃዋለህ ብዬ አላስብም።ስለዚህ አሁን የሄዱበት መንገድ ትክክል ነው ብዬ አላምንም።

ዘኢትዮፆያ- አንዳንዶቹ ይህን ስምምነት "ከወያኔ ጋር የማበር፣ መተባበሩ ሌሎቹን ተቃዋሚዎች በመቃወም ላይ የተመሠረተ" ግንኙነት አድርገው ነው የሚመለከቱት፣ ሌሎች ደግሞ "ወደ ወያኔ ጎራ እንደመግባት" አድርገው ነው እየወሰዱ ያሉት፣ እዚያ ደረጃ ታደርሰዋለህ?

አቶ ምርጫው- ወያኔ ሆኑ ለማለት እቸገራለሁ። ወያኔ ሆነዋል ለማለት በኔ አንደበት በጣም ይከብደኛል። የሆኖ ሆኖ ግን አንድ ሀቅ አለ፣ ለወያኔ ግን ዓላማ ማስፈጸሚያ መሣሪያ ሆነዋል።

ዘኢትዮጵያ-- ባለማወቅ ነው?

አቶ ምርጫው- ይህንን ባለማወቅ ልል አልችልም።

ዘኢትዮጵያ-- ባለማወቅ ከሆነ በማወቅ ነው?

አቶ ምርጫው- በማወቅ ወያኔን ለመጥቀም ነው እንኳ ባልል፣ እነዚህ ሰዎች፣ እነሱ በታያቸው፣ ጥሩ ነው ባሉት ለትግሉ ይረዳል ባሉት፣ ሄደው ሊሆን ይችላል። ግን እስከዛሬ ሁላችንም በተግባር ባየነውና የወያኔን ባህርይ ከተረዳነው ተነስተን ስንገምግም ይህ መንገድ ዛሬ የሚያደርጉት ነገር፣ በተለይ የተስማሙበት ሰነድ አለ። ምርጫ ቦርድን የበላይ ጠባቂና ወሳኝ አድርገው ተቀብለው ነው። የወያኔውን ምርጫ ቦርድ፣ በኃላፊነት ምርጫ ሳይካሄድ፣ አምነህ ከተቀበልክለት፣ በምርጫው ጉዳይ የሚነሱት ጥያቄዎች

መንግሥት ይቀርባል እየተባለ፣ በሰነድ ላይ አንተ ከፈረምክ፣ ከምርጫው በኋላ የሚወስኑልህ ምርጫ ቦርድና መንግሥት (ወያኔ) ናቸው። በሁለቱ ውሳኔ ለመተዳደር ለመስራት ከፈቀድክ ውጤቱ የመጨረሻ ውጤት ወያኔ የፈቀደው ብቻ ነው የሚሆነው።

ዘኢትዮጵያ-- አቶ ኃይሉ ወይም ድርጅታቸው ይህን አካሄድና አቅጣጫ አያስተውሉትም የሚል እምነት አለህ?

አቶ ምርጫው- እስከዛሬ ካራመዱት የኢንጂነር ኃይሉ አቋም ተነስቼ በምንም መንገድ እሳቸው ለወያኔ ይሠራሉ ብዬ አላስብም። በሌላ በኩል ግን አሁን የተቀበሉትን ሰነድ ሳየው፣ ከምን ተነስተው ለምን እንዴት ወያኔ ማንነቱን እያወቁ፣ እንዴት አድርገው በቀረችው በአምስት ወር ጊዜ ውስጥ፣ ህዝባዊ የሆነ ነጻ ውድድር ተደርጎ፣ እምነት ተጥሎበት፣ በነጻ ምርጫ እንቅስቃሴ ወያኔን እናሸንፋለን ተብሎ እንዴት እንደገቡ እንቆቅልሽ ነው። ምናልባት ኢንጂነር ኃይሉ እንዳሉት፣ እነሱ ውስጥ ሆነው የሚያዩት እኛ ዳያስፖራ ሆነን የማናየው የተሰራ ነገር ካለ፣ ምንድነው "ሽልም ከሆነ ይገፋል፣ ቂጣም ከሆነ ይጠፋል" ይባላል። በምናውቀው የወያኔ ሥር ተታለው ከሆነ ወይም አውቀው እንርዳው ብለው ከሆነ፣ የሰው ልጅ ማንነቱን ደብቆ ዘለዓለሙን አይኖርምና እርቃኑን በሚቀርበት ጊዜ፣ አብረን እንመለከተዋለን።

ዘኢትዮጵያ-- አሁን ኢንጂነሩ ስለ ዳያስፖራው የሰጡት አስተያየት አለ አንብበኸዋል እርግጠኛ ነኝ።

አቶ ምርጫ- አንብቤዋለሁ። በእውነት ለመጀመሪያው ጊዜ ኢንጂነር ኃይሉ፣ ይህንን ስለምን እንዳሉ እኔ አላውቅም። አሁንም ይቸግረኛል። ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነህ አንዳንድ መግለጫ ስትሰጥ፣ ያስቀቃል ምክንያቱም ማን መቼ በምን ጉዳይ ለምን እንዲህ ያለ መግለጫ እንደሚሰጥ አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም እሳቸው እንዳሉት እኛ ያለነው ውጭ ነን። በበነጻነት ነው የምንኖረው። እሳቸው እዚያ ውስጥ ሆነው ይህን ለምን እንዳሉ አላውቅም። ምክንያቱም ካወቅናቸው ጊዜ ጀምሮ እስኪፈቱ ድረስና መጨረሻ እስከተለያየንበት ድረስ ይነገሩን የነበረው፣ "እድሜ ለእናንተ በእናንተ ኃይል ነው" እያሉ ነበር። አሁን የናንተ መኖር አለመኖር ዋጋ የለውም

…ዳያስፖራ ሆይ ሆይ የሚለው ለአምስት ቀን ነው። ኢንተረስቲንግ የሆነ ሕይወት የማይኖር ሰው ዓላማ የሌለው ኑሮ የማይኖር ሰው ነው የሚጮኸው…"ያሉን ነገር አለ። ይሄ ሁሉ ተሰዶ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ፣ ዓላማ የለውም ብለው የእስከዛሬው ጩኸታችን ዓላማ ቢስ እንደነበር፣ በኢንጂነር ኃይሉ አንደበት ሲገለጽ መስማቴ፣ ምን ያክል እንዳሳዘነኝ ልነገርህ አልችልም። በተለይ ይህንን ወያኔዎች ነገ የሳቸውን አንደበት እየተጠቀሙ ምን ያክል በኛ ትግል ላይ በኛ የሙብት የነጻነት፣ የብልጽግና፣ የደህንነትና የአንድነት ጥያቄዎቻችን ላይ፣ ምን ያክል ሊስቁብን እንደሚችሉ ሳስብ አዝናለሁ። አልፎ ተርፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ በውጭ የሚደረጉትን ትግሎች፣ እሳቸውን የመሳሰሉ ሰዎች ትግሉ ዓለም አቀፍ እውቅናና እርዳታ አግኝቶ በኢትዮጵያ ትግልና እንቅስቃሴ ውስጥ፣ በኢትዮጵያ በሚካሄድ ማንኛውም የነጻነትና የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ ማሳረፍ እንዳንችል፣ መሪዎቻችን ናቸው ባልናቸው ሰዎች እነሱ እንዲህ ናቸው መባሉና መገለጹ እጅግ እጅግ በጣም አሳዝኖኛል።

ዘኢትዮጵያ-- እዚህ ላይ የሚታየኝ አንደኛ ቁጣ ያለባቸው የሚናገሩትንም ነገር ኃላፊነት በመውሰድ በድፍረት የመጋፈጥ እንዲያውም አልፎ ተርፎ የንቀት ዓይነት ነገር ነው ያየሁበት፣ እንደዚህ ታይቶታሃል?

አቶ ምርጫ- መቆጣት ካለባቸው መቆጣት ያለባቸው በመለስ ዜናዊ ላይ ነው። እኛ ላይ አይደለም መቆጣት ያላባቸው። ማዘን መተከዝ ማፈር መሸማቀቅ ካለባቸው ይህ ሁሉ መሆን ያለበት በመለስ ዜናዊ ነው። እኛማ ቅድም እንደነገርኩህ ዘበኞች ሆነን፣ መኪና እየጠበቅን፣ በረንዳ ላይ ፀሐይ እየተመታን፣ ፍዳችንን እያየን ከምናገኘው፣ ግማሾቻችን እኮ ቤት ሸጠን ነው ትግሉን የረዳነው። ግማሾቻችን እኮ ልጆቻችንን ቀመን የምናይበት ጊዜ እስከምናጣ ድረስ ልጆቻችንን ሳናይ ሌትና ቀን እየዳከርን ነው። ግማሾቻችንኮ በብርድና በፀሐይ ስቴት ዲፓርትመንት ኮንግረስ በር ላይ በየስትሪቱ እንቅልፍ አጥተን እያደርን ነው። በእውነት እኮ ብዙ ኢትዮጵያዊ ሻሂ እየቀዳ፣ በእኔ እጅ እኮ እኔና ጓደኞቼ ሆነን ከ240ሺ. ዶላር አዋጥተን እንደሰጠናቸውኮ ያውቃሉ። ያ ገንዘብ የምርጫው ገንዘብ አይደለም። ወይም የአንድ የሁለት ሶስት ሰዎች ገንዘብ አይደለም። ዛሬ እንደዚህ የሚያበሻቅጧቸው ኢትዮጵያውያን ደምና ጉልበትኮ ነው። እንዴት መቆጣት? በኛማ መኩራት ነው የነበረባቸው። በሌላ በኩል ግን ይሄ ሁኔታ የከፈተውም እድል አለ። ሁሉም ለበጎ ነው የሚባለው።

ዘኢትዮጵያ-- ምን ዓይነት እድል ምንድነው የከፈተው?

አቶ ምርጫው- ቅንጅት አለ እየተባለ እነ እገሌ አሉ እየተባለ፣ ብዙ ኢትዮጵያን የሚሉ ሰዎች፣ ተቀብረው ተቀምጠዋል። መንቀሳቀስ እንኳ ሲጀምሩ፣ የለም የለም እነ አቶ ኃይሉ አሉ፣ እነሱን እንርዳ፣ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ አለ እነሱን እንርዳ፣ እነሱ እያሉ እየተባለ ብዙ እንቅስቃሴዎች እንዲታፈኑ ተደርገዋል። ዛሬ እነዚያ ሁሉ በየአቅጣጫቸው ሰብረው ይወጣሉ። ኢትዮያን የሚለው ኃይል በዚህ አጋጣሚ ይንቀሳቀሳል። ማለት ከዚህ በኋላ ብዙ አንጋጦ የሚጠብቀው ተስፋ ላይኖር ይችላል በሰውየው ላይ።

ዘኢትዮጵያ-- አምባገነን ናቸው ይሏቸዋል

አቶ ምርጫው- አንድ ነገር ላንሳልህ ለምሳሌ መንግሥቱ ኃይለማርያም፣ መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው እንደዚህ ነው ይባላሉ። አካሄዳቸውን አመጣጣቸውን ተመልከተው- የሚመሳሰል ነገር ታያለህ። እዚህምጋ ለምሳሌ ከኢንጂነር ኃይሉ ጋር ፕሮፌሰር አስራት በጭራሽ አይዋደዱም ነበር። በእሳቸውም ምክንያት ነው የለቀቁት ይባልም ነበር። ከወጡ በኋላ አቶ ኃይሉን እንዲመለሱ

ይደረጉት አሊ እድሪስ ናቸው። አሊ እድሪስ የታሉ ዛሬ? አሊ እድሪስ እንደወጡ እንዲቀሩ የተደረጉበት ምክንያት ምንድነው? አብረዋቸው የነበሩት እነ ወንዳየሁ ካሳ ነበሩ፣ ወንዳየሁ ካሣ ዛሬ የት ናቸው? በአቶ ኃይሉ ነው የተባረሩት፣ እነ ሻለቃ አድማሴ  በኢትዮጵያ ትግል ያን ያህል ዘመን ሲጨኹ የነበሩ ሰዎች ናቸው፣ አቶ ኃይሉ አንድ ጋዜጣ ላይ ቃለ መጠይቅ ሲሰጡ ሻለቃ አድማሴን “እንጣጥ እንጣጥ ይላል” እያሉ እያወረዱ ነው ያፈረጧቸው። እነዚህ ሁሉ ሰዎች፣ እና በአመራሩ ዙሪያ የነበሩ ሰዎች የታሉ? ዛሬ እሳቸው ዙሪያ ስላሉት ከሻለቃ ጌታቸው እና አንዳንድ ፓልቶኮች የሚወጣው ማሙሽት ከሚባለው ሰው ሌላ ጥራልኝ ብልህ በዙሪያው ስንት ሰው ትጠራልኛለህ?

ዘኢትዮጵያ-- ስለዳያስፖራው ሲናገሩ ምንም እንደማያመጣ፣ ምንም አቅም እንደሌለው ነው የተናገሩት ዳያስፖራው አቅም አለው ብለህ ታስባለህ?

አቶ ምርጫ- ዳያስፖራው አቅም አለው። ጋሽ ኃይሉ፣ በእውነት በዚህ እንደናቁን አይደለንም። አቅም አለን። አቅማችንን ከሞላ ጎደል በመሳተፍ አውቀዋለሁ። ኢትዮያጵያዊ ሲሳተፍ የሚበጀውን መሪ ሲያገኝ፣ እንዴት እንደሚንቀሳቀስ እንዴት እንደሚቆም አይቻለሁ። እሳቸውም እንደሚያዉቁት ለምሳሌ ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ባቋቋመው፣ በትንሳኤ ሬዲዮ፣ እስር ቤት ሆነው ምን ያክል በዚህ ጉዳይ ይደሰቱ እንደነበር ይነግሩን ነበር። ነገ ሬዲዮ ቢቋቋም አገር ውስጥ የሚገባ ነገር ለማድረግም ሆነ አለ ለሚባል ነገር ሁሉ ፈጥነን መድረስ እንደምንችል አውቀዋለሁ። ከሁሉ የሚያሳዝነው የሳቸው ማሳዘን ሳይሆን ሰድበው ለሰዳቢም ሰጥተውናል። የእነሱን ትችት አዲስ አበባ ሎካል ጋዜጦች ካንፀባረቁት አዲስ አበባ ይደርሳል፣ ከአዲስ አበባ ግን በጭራሽ አያልፍም መንገድ ላይይቀራል ፣ በእኔ ላይ ደግሞ የሚፈጥረው የለም።” ነው የሚሉት በግላቸው ነው ። እንዴት በኔ ላይ እንዲህ ያለ ነገር አይፈጥርም ብለው እንዳሉ አላውቅም። ምክንያቱም የሚወራውኮ ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ነው። ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ሲወራ ለምንድነው በኔ ላይ የሚባለው። ይሄ ሁሉ ኢትዮጵያዊ እኮ በረንዳ ላይ እያደረ፣ በብርድ እየተሰቃየ፣ ይጮህ የነበረው፣ በርግጥም ብሶቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ አጋርነቱን ብሶቱን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እያደረሰ ምን ያህል ወያኔን አስጨንቆት እንድነበር እስከ ቅንጅት መፍረክረክ ድረስ፣ ውጭ ያለው የዳያስፖራው ጉልበት ምን ያክል እንድነበር እናውቃለን። “አዲስ አበባ ያለውን ሁኔታ ተቆጣጥረናል የሚቀረን ውጭ ያለውን መቆጣጠር ነው ይሉ ነበርኮ” እነመለስ። ዛሬ ግን በተወሰነ ደረጃ አዎ ምናልባት መስሏቸው ይሆናል። ሶስት አራት ሰዎችን እነመለስ ሰብስበውም ጨብጠውም ስላወሩ፣ የነሱ አቅም ባዶ ነው ብለው ይሆናል፣ ይልቅስ ለሳቸውም ቢሆን ይረዳ የነበረው፣ ይህንን አቅም ይዘው መደራደሪያ ቢያደርጉት ነው። ከዚህ ሁሉ አቅም ተነጥለው ብቻቸውን እዚያ ቆመው መለስ ጋር ሰጥቶ መቀበል፣ የሚባለው ነገር፣ ምን እንደሚሰጣቸው መለስ ያውቃል፣

ዘኢትዮጵያ- -ምርጫው ብዙ ጊዜ ህብረት ሲቋቋም፣ ቅንትጅ ሲቋቋም እንደዚህ ድርጅቶች ለአንድ ነገር በጋር ለማበር በሚጥሩበት ጊዜ የማፍረስ ነገር ይሠራል፣ በተቃራኒነት ይቆማል፣ፖለቲካ ስሜቱ በተሟሟቀ ጊዜ በአፍራሽነት ይሰማራል፣ ብለው የሚከሱህ ሰዎች አሉ ክሱን ሰምተኸዋል?

አቶ ምርጫው- አንተ ነህ አንደኛው፣ አንተ ነህ የጠየቅከኝ የነበረው፣ ይሄ ህብረት በሚቋቋምበት ጊዜ ነበር እና...

ዘኢትዮጵያ-- ከሳሹ አንተ ነህ እያልከኝ ነው?

አቶ ምርጫው- አያይ አይደለም። ጠይቀኸኝ ነበር ማለቴ ነው። ሰምተኻል ወይ ብለህ ስትለኝ ጠይቀየኸኝ መልስ ሰጥቼህ ስለነበረ ነው። እና...

ዘኢትዮጵያ-- ከኔ ውጭ አልሰማኸውም?

አቶ ምርጫው- አይ እሱስ ይባላል።... እና ግን ትክክለኛ ህብረት ነው ብዬ በማምንበት ጊዜ የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነትና ህልውና ያስረገጡ የፖለቲካ ድርጅቶች እንቅስቃሴ በሚሆንበት ጊዜ ደግፌያለሁ። ከማንም በላይ ጊዜዬን ጉልበቴን ገንዘቤን አጥፍቼ ደግፌያለሁ። በውስጡ ደግሞ ኢትዮጵያዊነቱን የሚያፈርሱ ኢትዮጵያን የሚጠሉ፣ የሚጠየፉ ኃይሎች ሲሆኑ ሁልጊዜም እቃወማለሁ። ለምሳሌ ባለፈው ከህብረቱ በኋላ ቅንጅት ተቋቁሟል። ቅንጅትን ከማንም በላይ፣ በግለሰብ በምርጫነቴ፣ በሬዲዮናችን በኢትዮጵያዊነት፣ ሸንጣችንን ገትረን ቅንጅትን በግንባር ቀደም ከደገፉት መካከል አንዱ እኛ ነን። በሌላ በኩል ለምሳሌ ኤ ኤፍ ዲ ተቋቁሞ ነበር። ኤ.ኤፍ.ዲ እነ ኢንጂኔር ኃይሉ ታስረው፣ የተቋቋመ ድርጅት ነበር። በኬ አይ ኤል ቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ተብሎ የተቋቋመ ነበር። ያን ጊዜ የነበሩት የግንጠላ ኃይሎች፣ በሙሉ በሻእቢያ አስተባባሪነት፣ የጀመሩት እንደነበር፣ መረጃው ስለደረሰን ኤ.ኤፍ.ዲን ቅንጅት ራሱን ችሎ መቆም የሚችል ድርጅት ነው። ምን ጊዜም ቢሆን ግንጠላን ያስቀደሙ ድርጅቶች ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነትን ሊያመጡለት አይችሉም። ዓላማቸው በፖለቲካቸው ደግፈው የሚንቀሳቀሱት መገንጠልን ነው። መገንጠልን ደግሞ እንዋጋለን። ስለዚህ አቅም በፈቀደ መጠን ይህ ነገር መፍትሔ የለውም። ትክክል አይደለም። የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት አያመጣም በሚል ተቃውመናል። ለምሳሌ እነሰዬ እነገብሩ አስራት የመሠረቱት መድረክ የሚባል አለ። ምንድነው አንድ የሚባል አባባል አለ። “የሚጠጣ ውሃ ቢጠፋ መርዝ አይጠጣም” ይባላል። ሁለተኛ ከገብሩ አስራት ጋር ሆኜ የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት አመጣለሁ ብዬ ላስብ አልችልም።

ዘኢትዮጵያ-- እንግዲህ ሁሉንም አየህ፣ አቶ ኃይሉንም አየህ አሁን ባንተ ዓይነ ሜዳ ያላ ድርጅትም ሆነ የፖለቲካ ሰው ማነው?

አቶ ምርጫ- ኢትዮጵያ በጣም ትልቅ አገር ናት ። ቅድም እንደነገርኩህ በኃይሉ ሻውል ዙሪያ ለመሰለፍ የተዘጋጀ በጣም በርካታ ሰው ነበረ። የቅንጅት መከፋፈል የሚባል እስከመጣበት ጊዜ ድረስ፣ በአካል ብዙ ሰዎች አውቃለሁ። ብቃት ያላቸው ብዙ ሰዎች አሉ። እንቅስቃሴ እንኳ መፍጠር እየፈለጉ የለም ያለውን ማጎልበት ነው የሚያስፈልገው እየተባለ፣ በተለያየ መንገድ እየገፈተሩ፣ በተለያዩ ግለሰቦች እየተገፈተሩ፣ ወደ ትግሉ ያልመጡ ሰዎች አሉ። አሁንም በዚህ ፓርቲ በዚህ መንገድ እንውጣ ብለው። አሁንም እነዚያ እያሉ እንዴት እንደዚያ ዓይነት ነገር እንፈጥራለን ተብለው ተቀመጡ ቆዩ እየተባሉ በየ አቅጣጫው ብዙ ሰዎች በዚያ ሁኔታ ተቀምጠዋል። መሸጎ ማለቴ ነው። ያ አሁን ከ የአቅጣጫው ይወጣል ይፈነዳል። እስከዛሬ ካለው አጠቃላይ እንቅስቃሴ ልብ አድርግ፣

ዘኢትዮጵያ- - አሁን የሬዲዮ ፕሮግራምህ እንድቀጠለ ነው?

አቶ ምርጫው - አዎ ኢትዮጵያዊነት ሬዲዮ አለ። ዘወትር እሁድ በ1390 ከ3.30 እስከ 5ፒ ኤም ይደመጣል።